# ዓላማ መር ቤተሰብ

የአንድ ሃገርና ህብረተሰብ መጀመሪያ ቤተሰብ እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው፤ ይህ ቤተስብ ሲመሰርት ራሱን የቻለ አጀማመር አለው። እንደክርስቲያን የምናምነው ቤተስብ የተመሰረተው በሰራዊት ጌታ በእግዚአብሄር የእጅ ስራ ብቻ እንደሆነ ያለ ጥርጥር እናምናለን። ይህም ጋብቻ በሚል ይጀምራል።ጋብቻ የኖረበት ምክንያት የእግዚአብሄርን ማንነትና ሏላዊነት ለማስፋፋት ለእርሱ ክብር እንዲሆንና የእርሱን መልክ ለማንጸባረቅ የተፈጠረ ተቋም ነው፤

ጋብቻን እግዚአብሄር ሲሰራው እስከ መጨረሻው እንዲቆይ አድረጎ ሲሆን መከፋፋት አለመስማማትና አድጎም መለያየት የሚያመጣው ከአላማው ውጪ በምንጓዝበት ጊዜ ነው። በጋብቻችን ውስጥ ከአላማው ውጪ እየተጓዝን ደስታና ሰላም በምናጣበት ጊዜ እንዲሁ በመከራ እንኖራለን ወይንም ትዳራችንን እናፈርሳለን። ከፍተኛ ፐርሰንት ያላቸው ትዳሮች የሚፈርሱት አላማቸው በእግዚአብሄር አላማ የተቀረጸ ሳይሆን እርስ በርሳቸው በተያያዙበት ምክንያት ነው፤ ለምሳሌ በመዋደድ፣ በኢኮኖሚ፣ ወይንም ኑሮን በጋራ ለመወጣት ሲሉ ይጣመሩና፣እነዚህ ነገሮች ቀስ እያሉ ከነበራቸው ሁኔታ እየወረዱ ሲመጡ በባልና በሚስት መካከል አለመግባባትን ይፈጥሩና ትዳራቸው የመፍረስ አደጋ ያጋጥመዋል፤

በእግዚአብሄር መንግስት አላማ ውስጥ የተጠቀለሉ ባለትዳሮች ስለፍላጎታቸው ፣ ስለስሜታቸው፣ስለ ግላቸው አላማና ፈቃድ ሳይሆን እግዚአብሄር በጋብቻ ውስጥ ስለ አለው አላማ (PURPOSE ) ስለሚኖሩ እስከ ሞት ድረስ ጸንተው ይኖራሉ፤ ጋብቻ social contract አይደለም ቅዱስ የሆነ እስከ መጨረሻው የሚጸና ቃል ኪዳን ነው፤ ስኬትን ለማግኘት፣ የስሜት እርካታን ለማግኘት ወይንም ስም ለማግኘት ተብሎ የተሰራ መሳሪያ አይደለም፤ ጋብቻን በሰራው በእግዚአብሄርና በምእመናን ፊት ቃል ኪዳን ገብተን እንደፈቃዱ አብሮ ለመኖር በተነገረው የእግዚአብሄር ቃልና በሚደረገው ባርኮት መሰረት በፍቅር፣ በመከባበር፣በህመምና በጤንነት፣ በሃብትና በድህነት፣በመልካምና በመጥፎ ጊዜያቶች አብሮ በመረዳዳት ለመኖር የገባነውና የምንገባበት ተቋም ነው፤ ይህ ቃል ኪዳን ግን በየጊዜው ሲፈርስና ትዳር ሲበተን እናያለን፤ በተጨማሪም ከእንደዚህ አይነት ቤት ውስጥ የሚወለዱና የሚያድጉ ልጆች ስለ እምነት ያላቸው እይታ፣ ስለራሳቸው ያላቸው ማንንነት ያዘቀተ ስልሚሆንና ወደፊትም ሰለ ጋብቻ ያላቸው አመለካካት የተበላሸ ስለሚሆን ጠንካራ ትዳር ሊመሰርቱ አይችሉም፤

በዘመናችን የብዙዎቻችን ጋብቻ በውስብሰብ ችግሮች ውስጥ እየገባና አደጋ ላይ እየወደቀ ለመፍረስ ጫፍ ላይ የደረሰበትና ደግሞም የፈረሰበት ምክንያት በመጸሃፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጠውን እውነት አጥርተን ማየት ስላልቻልንና በጋብቻ ውስጥ የሚገኘውን በረከት በቅጡ ካለመረዳታችን ነው። በጋብቻ ውስጥ ያለው የእግዚአብሄር አላማ (PURPOSE )ና መመሪያ (PRINCIPLE ) ሲናቅ የእርሱ መልክ ወይንም ተምሳሌነት ይዛባል፤

**የእግዚአብሄር መንግስት ጋብቻ ማለት "በወንድና በሴት መካከል የሚፈጸም ቃል ኪዳናዊ ትስስር ሲሆን ይህም በእግዚአብሄር መለኮታዊ ስልጣን ስር ህብረት ለማድረግ ራሳቸውን የሰጡና የእግዚአብሄርን መልክ *(IMAGE )* አገዛዙን *(RULE )* በግል ይሁን በጋራ ጥሪያቸው ለማስፋፋት እንዲቻል ተደርጎ የተቀራኘ ህብረት ወይንም ተቋም ማለት ነው"፤**

ስለዚህ በጋብቻችን ውስጥ ይህ መታየት አለበት፣ መዋደድን ሳናሳንስ፣ መከባብረን ሳናሳንስ፣ መረዳዳትን ሳናሳንስ የምናደርጋቸውን ማናቸውም ነገሮች ለእግዚአብሄር ክብር እንደሚሆኑ በመረዳት የእግዚአብሄር የበላይነትንና አላማውን ልናስፋፋ የተጋባን መሆናችንን ልንረዳ ይገባል፤

ይህ ደግሞ ሊሆን የሚችለው የእግዚአብሄር መንግስት ምንነት ሲገባንና ባልና ሚስት የእያንዳንዳቸውን ሃላፊነት ሲወጡ ብቻ ነው፤ አንድ ሰው ለተወለደበት ሃገር ዜጋ እንደሚሆን ሁሉና በተወለደበት ሃገር ስልጣንና አገዛዝ ስር እንደሚሆን እኛም በክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በሚገኘው የዘላለም ህይወት በማመን ዳግም ተወልደናል፤ ስለዚህ ለተወለድንበት መንግስት ዜጋ ስለሆንን በእርሱ ስልጣንና አገዛዝ ስር እንሆናለን ማለት ነው፤" **በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" ዮሃንስ *3፡16***

**"ደግሞም ኢየሱስ። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።" ዮሃንስ *8፡16***

ስለዚህ በክርስቶስ የዳንን ሁሉ የዚህን መንግስት የህይወት ብርሃን ልናበራ ይገባል፤ ከዘፍጥረት እስከ ራእይ የሚናገርው በሙሉ ስለ እግዚአብሄር ክብርና ስለ መንገስቱ የበላይነት ነው፤ ወደ እግዚአብሄር የቀረበና የተጠጋ በትእዛዙ በቃሉ የታሰረ ጋብቻ ሰረአት ያለው፣ ውጤትና ስኬት ያለው ይሆናል፤ እግዚአብሄርን ከመሃከላችን አስወጥተን፣ ቃሉን ሸረን ስረአቱን አጥፍተን እንኖራለን ብንል የተተራመሰ (chaos ) አናርኪሲዝም የሞላበት ቤት ይሆናል፤ የእግዚአብሄር

መንግስት በፍጥረት ሁሉ ላይ ሙሉ በሙሉ የሚገዛ ነው፤**“እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥ መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።” መዝሙር *103፡ 19***

ማንኛውም መንግስት ሶስት ዋንኛ አካል ይዟል፤ ገዢ፣ ግዛት፣የአገዛዙ ስርአት ወይንም መመሪያ አለ እያንዳንዱ ተገዢ በዚህ ስልጣን ስር ይወድቃል፤ ይህ ሰራት የሌለው መንግስት፤ መንግስት ነው ማለት አይቻልም፤ መንግስትም የለም፤ ሰራት አልበኝነት የነገሰበት ስብሰብ ይሆናል፤ እኛ በክርስቶስ የዳንን ሁሉ የእግዚአብሄር መንግስት ባልደረቦች የሰማያዊው መንግስት ወራሾች ነን፤ አገራችንም በሰማይ ነው፤ጌታ እየሱስ ከስቃዩ በፊት ለጲላጦስ ስለ መንገስቱ ሲናገር **“ጲላጦስ መልሶ። እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ወገኖችህና የካህናት አለቆች ለእኔ አሳልፈው ሰጡህ፤ ምን አድርገሃል? አለው።” ኢየሱስም መልሶ። መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው።” ዮሃንስ *18፡35_36***

እየሱስ ክረስቶስ መንግስቴ ከዚህ አይደለም ካለ ወገኖቼ እኛም ከዚህ አይደለንም፤ በዚች ምድር የእግዚአብሄር መንግስት ኪዳን ያለቸው 3 ተቋሞች አሉ ቤተሰብ፣ ቤተክርስቲያንና የሲቪል መንግስት፤ እነዚህን ሁሉ እግዚአብሄር ይገዛቸዋል፤ተጠሪነታቸውም ለእርሱ ነው። የእርሱን አመራር ተቀበሉም አለተቀበሉም፣ራሳቸውን ስጡ አልሰጡም ባለስለጣኑ እርሱ እግዚአብሄር ነው፤ እነዚህ ሶስት ተቋሞች ቤተስብ፣ ቤተክርስቲያን፣ የሲቪል መንግስት የተሰሩት (design )የተደረጉት በፍጹም እውነት ላይ ተመስረተው ተገባራቸውን እንዲያከናውኑ ነው፤

በዚህ ስልጣን ስር ሆነው መከናወን ካልቻሉ መፈራረስን፣ብልሹንትንና ዋልጌነትን ፣ መበታተንንና መለያየትን ያስከትላሉ፤ ልክ በኤደን ገነት በአዳምና በሄዋን ላይ የደረስው አይነት ይሆናል፤ እግዚአብሄር ለአዳምና ለሄዋን በገነት ውስጥ የሰጣቸው ትእዛዝ እዛ ካሉት ዛፎች በሙሉ በነጻነት እንዲበሉ ሲሰጣቸው መልካሙንና ክፉውን ከምታስታውቀው ዛፍ ግን እንዳይበሉ አዟቸው ነበር፤ ምክንያቱም የእርሱ መገለጥና እውነት የህብረታቸው መሰረት እንዲሆን እንጂ ለራሳቸው ፈቃድና ምርጫ ተላልፈው እንዳይሰጡ ስለሚፈልግ ነው።

በጋብቻችን ውስጥ የምናደርጋቸው ውሳኔዎች በሙሉ ፍጹም እውነተኛና ትክክለኛ ምክንያት ያዘሉ መሆናቸውን ልናረጋግጥ ይገባል፤ ፍጹም እውነተኛና ትክክል ደግሞ እግዚአብሄርን መሰረት ያደረገ እውቀትና መረዳት ነው።

ሌላው ደግሞ ፍጹም በሆነ እውነተኛ መሰረት ላይ ብቻ ሳይሆን ክብሩ ለእግዚአብሄር ስለሚሆንም ጭምር **ነው፤"እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።" *1ኛ ቆሮንቶስ 10፡31***

**"ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።" ሮሜ፡*11፡36***

ህይወታችንን በእግዚአብሄር ስልጣንና ሃላፊነት ሰር ስናስቀምጥ በእርሱ ያለው ክብር በእኛ በኩል ይገለጻል፣ ይንጸባረቃል፤ ህይወት ይበዛልናል ይትረፈርፍልናለም፤ **"ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።" ዮሃንስ ወንጌል *10፡10***

የእግዚአብሄርን ክብር ለማምጣት ትዳራችን ወይም ጋብቻችን ለእግዚአብሄር ሏላዊነት ስልጣን ስንገዛ ብቻ ነው፤ ይህ እውቀትና መረዳት በየትኛውም የህይወት አቅጣጫ ላይ የሚሰራ ነው፤ ይህ በህይወታችን ሲፈጸም የእግዚአብሄር የበረከት እጁ ይዘረጋል፤ "**እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።"ሮሜ 8፡28**

የብዙውቻችን ጋብቻ ችግር ላይ የሚወድቀው በትግል ውስጥ የሚያልፈውነገር ግን በእግዚአብሄር ቃል መሰረት የማንመራ ከሆነ የማንቀበለው የማንታዘዘው ከሆነ የበረከት እጁን የነገሮችን ወደ በጎና መልካምነት መለወጥን እናጣቸዋለን። እግዚአብሄር ስለ ጋብቻችን ካዘጋጀው አጀንዳ ይልቅ የራሳችንን አጀንዳ ለማስፈጸም ስንጥርና ይህንንም አጀንዳችንን እንዲባርክልን ፣ የእርሱን ፕላን ትተን የራሳችንን ፕላን ቀጥሉ እንዲለን በመፈለግ፣እርሱ በሰራው ጋብቻ ውስጥ ባሰመረልን የህይወት መንገድ በመኖር እርሱን አክብረን እርሱ በትዳራችን ከፍ ብሎ እንዲታይና እንዲከብር ከመፈለግ ይልቅ እኛን ከፍ እንዲያደርገንና እንዲያከብረን በመፈለጋችን ነው። ታዲያ እግዚአብሄር አንድ ወንድንና አንድ ሴትን በጋብቻ ሲያስተሳስራቸው አላማው ምንድ ነው?

እግዚአብሄር ሰውን ከፈጠረ በኋላ ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም አለ " **እግዚአብሔር አምላክም አለ። ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።**
**እግዚአብሔር አምላክም የምድር አራዊትንና የሰማይ ወፎችን ሁሉ ከመሬት አደረገ፤ በምን ስም እንደሚጠራቸውም ያይ ዘንድ ወደ አዳም አመጣቸው፤ አዳምም ሕያው ነፍስ ላለው ሁሉ በስሙ እንደ ጠራው**

**ስሙ ያው ሆነ። አዳምም ለእንስሳት ሁሉ፥ ለሰማይ ወፎችም ሁሉ፥ ለምድር አራዊትም ሁሉ ስም አወጣላቸው፤ ነገር ግን ለአዳም እንደ እርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር። እግዚአብሔር አምላክም በአዳም ከባድ እንቅልፍን ጣለበት፥ አንቀላፋም፤ ከጎኑም አንዲት አጥንትን ወስዶ ስፍራውን በሥጋ ዘጋው። እግዚአብሔር አምላክም ከአዳም የወሰዳትን አጥንት ሴት አድርጎ ሠራት፤ ወደ አዳምም አመጣት። አዳምም አለ። ይህቸ አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት፤ እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል፤ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ። አዳምና ሚስቱ ሁለቱም ዕራቁታቸውን ነበሩ፥ አይተፋፈሩም ነበር።"ዘፍ*2፡18_25***

እግዚአብሄር ወንድና ሴትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተሳሰረው በኤደን ገነት ውስጥ ነው፤ ይህንን ሲያደርግ ኣላማው ሁለት ነው፤

**1ኛ፣ እንዲበዙ**

**2ኛ፣ እንዲገዙ**

እንዲበዙ ሲል ልጆቸን እንዲወልዱ፣ እንዲስፋፉ ማለት ነው

እንዲገዙ ሲል በፈጠረው ፍጥረት ላይ ሁሉ ገዢ እንዲሆኑ እንዲሰለጥኑባቸው ፤ እንደ እርሱ ሆነው፣ ወኪል ሆነው፣ አምባሳደር ሆነው እንዲያገለግሉት ማለት ነው፤

ይህንን መፈጸም የሚቻለው ወንድና ሴት አድረጎ በመፍጠር ሲሆን ይህም በዘፍጥረት 2፡18_25 ላይ ተገልጿል፤ እግዚአብሄር ከአዳም አጥንት በመውሰድ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት ብሎ ሄዋንን ፈጠረ፤ እንደርሱ ያለ ረዳት አልተገኘለትም ነበር ፤ ይህም ማለት እርሱን የሚመስል ፣ እንደርሱ የሚያሰብ፣ የእግዚአብሄር እስትንፋስ ያለበት ማለት እንጂ ለፍጥረትማ እነ አንበሳ እነ ነበር እነ አውራሪስ ነበሩ አዳምን ከእነዚህ ጋር አጣምሮ እግዚአብሄር አላማው እንዳማይፈጸም ያውቅ ስለ ነበረ ነው፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት ሲል፣ እግዚአብሄር ለአሰበው ሃሳብ፣ ለአላማው አብራው የምትሰራ የምትረዳ፣ ተባብረው እግዚአብሄር ለፍጥረት ሁሉ ያለመውን ሊሰራ ያቀደውን በቲም ወይንም በቡድን ሆነው እንዲሰሩ ለማድረግና እረስበርሳቸውም እንዲረዳዱ ጭምር ነው። ወደ አዳምም አመጣት ሲል ለአዳም ሰጠው ይቹትልህ

የምትረዳህ ማለቱ ነው ልክ ዛሬ እኛ እግዚአብሄር ስጠኝ እንደምንለው ማለት ነው።

ጋብቻ ሲጀመር አጥንት ከጎን ውስጥ በማውጣት ነበር አሁን እንደሱ በማድረግ አይደለም እግዚአብሄር ሚስት ወይንም ባል የሚሰጠን በመስህብ ነው ማለት በ attraction፣ በውበት፣ በቁመና በቁምነገርኝነት፣ በንግግር፣ በአለባበስ፣ በመንፈሳዊ ህይወት፣ ብቻ በአንድ የመስህብ ሃይል ተስበን እንጋባለን፤ አዳምም ያለው አጥንት ከአጥንቴ ናት ስጋም ከስጋዬ ናት ብሎ ወደ ራሱ አመጣት ወይንም ወሰዳት፤ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ስጋ ይሆናሉ፤ እንግዲህ ጋብቻ በዚህ ሁኔታ በእግዚአብሄር የተመሰረተ ሲሆን አላማውም ከገዢነት ጋር ቀጥታ  ግንኙነት ያለው ነው፤

## አንድ ስጋ ይሆናሉ፣

የመጀመሪያው አንድነት፦ የመንፈስ አንድነት ነው፣ በእግዚአብሄር መንፈስ ተፈጥረዋልና፤ የመንፈስ አንድነት አላቸው፤ ልክ እኛ በክርስቶስ አንዱን መንፈስ እንድጠጣን ማለት ነው፡

ሁለተኛው አንድነት፦ በአጥንትና በስጋ ተገናኝተዋል፣ በሩካቤ ስጋ (sexual intimacy ) ጥምረት አላቸው ከአብራካቸው የሚወጡ ትውልዶች አሉ፤ እኛም በመስህብ እንቆራኛለን በፍቅር ደስታ ውስጥ እንገባለን በሩካቤ ስጋ (sexual intimacy )እንጣበቃለን ከአብራካችን የሚወጡ ትውልዶች ይፈጠራሉ (new generation)

ይህንን አንድነት ጌታ እየሱስ ክርስቶስ በማቲውስ ወንጌል 19፡1_8 ለፈሪሳውያን ሲነግራቸው እናያለን።

**“እየሱስም ይህን ነገር ከፈጸመ በኋላ፥ ከገሊላ ሄዶ ወደ ይሁዳ አውራጃ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ መጣ። ብዙ ሕዝብም ተከተሉት፥ በዚያም ፈወሳቸው።ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡና ሲፈትኑት። ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት። እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ። ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥ አለም። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን? ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው። እነርሱም። እንኪያስ ሙሴ**

**የፍቾዋን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቱአት ስለ ምን አዘዘ? አሉት። እርሱም። ሙሴስ ስለ ልባቸሁ ጥንካሬ ሚስቶቻቸሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላቸሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።”**

## ለምን አንድ አደረገን?

- ቀደም ሲል እንደ ተገለጸው በአንድ መንፈስ የመንግስቱን አላማና ሃሳብ ማስፈጸም እንድንችል፤
- እርስ በርሳችን እንድንረዳዳ፤
- በፍትወት እንዳንቃጠል እርስበርሳችን ደስ እንዲለን፤
- ሌላው በመብዛት ውስጥ የሚፈጠር ታላቅ የሆነው የእርሱ ስራ በምድር ሁሉ እንዲበዛ ከአብራኮቻችን የሚወጡት ልጆቻችን እግዚአብሄርን የሚፈሩና የሚቀጥለውን የእግዚአብሄር መንግስት ስራ ይዘው እንዲሮጡ ለማድረግ ነው፤ ሚልኪያስ2፡15_16

  *“እግዚአብሔር አንድ አላደረጋቸውምን? በሥጋም በመንፈስም የእርሱ ናቸው። ለምን አንድ አደረጋቸው? ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለውን ዘር ይፈልግ ስለ ነበር ነው። ስለዚህ በመንፈሳቸሁ ራሳቸሁን ጠብቁ፤ ከወጣትነት ሚስታቸሁም ጋር ያላቸሁን ታማኝነት አታጓድሉ።”*

ስለዚህ ወገኖቼ ዛሬ ከሚስታችን ከባላችን ጋር አንድ ያደረገን እግዚአብሄር ለእርሱ ታላቅ አላማ መሳርያ እንድንሆንለት እንጂ እርስብረሳችን እየተያየን በጎደለና በሞላ፣ በማድረግና ባለማድረግ ላይ የተመሰረተ፣ የራሳችንን ጥቅም የምናስፈጽምበት ተቋም ወይም ጥምረት አይደለም፤ ልንነቃ ይገባል።

ሰይጣን አዳምንና ሄዋንን ያሳተው በዛፍ ፍሬ ነው፤ ዛሬ የሚያስተን በዛፍ ፍሬ አይደለም በተለያዩ ከግል ፍላጎት ጋር የተያያዙ ፍሪዎቸ እያቀበለን ልክ አዳምና ሄዋን እግዚአብሄር የሰጣቸውን ትእዛዝ ጥለው ለራሳቸው ፈቃድ እንደተገዙ ዛሬም በትዳራችን ሰይጣን የሚያደርገው ለራሳችን ፈቃድ እንድንገዛ የሚያደርጉንን ፍሬዎቸን በገበታ ላይ ስለሚደረድርልን ነው፤

የእግዚአብሄርን በጎነት እንዳንናገር፣ የእርሱ ካህን መሆናችንን እንዳንገልጥ እዚያው ጨለማ ውስጥ እንድንዳከር ለማድረግ ነው። የእግዚአብሄር ወገን መሆናቸን በምድር ሁሉ እንዳይታወቅ እባልንና የሚስትን ህይወት በማጠልሸት ትዳራችን እንዲበተን ልጆቻችን ያለ አባት ወይንም ያለ እናት እንዲቀሩ

ለማድረግ ፣ ምስክርነታችን እንዲጠፋ፣ የእግዚአብሄር ስም እንዲሰደብ ለማድረግም ጭምር ነው፤

በ1ኛ ጴጥሮስ 2፡9_10 ላይ እንዲህ ይላል "**እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል። ወዳጆች ሆይ፥ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፤ ስለሚመለከቱት ስለ መልካም ሥራችሁ፥ ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፥ በሚጎበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።"**

ይህ በትዳራችን ህይወት ውስጥ እንዲገለጥ ምን ማድረግ አለብን?

- ወደ ትክክለኛው የእግዚአብሄር ሃሳብ መመለስ
- እርስበርስ መታረቅ፣ መስማማት፣ ንስሃ መግባት በአዲስ መስመር መጀመር
- እግዚአብሄርን የሚፈራ ትውልድ ለማፍራት ደግሞም ለመምራት የእኛ መንፈሳዊ ህይወት ወሳኝ ስለሆነ በቃል፣ በኑሮ በአገልግሎት መገለጥ መቻል አለበት
- ከእምነታችን የተነሳ የምናደርገውን መታዘዝ መፈጸም መቻል አለብን፤ **"በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን፤" ሮሜ*1፡5***

  ባልና ሚስቶች የተጻፈላቸውን የእውነት ቃል ያለምንም ማመቻመች ማንኛውንም ዋጋ በመክፈል በህይወታችን በመለማመድ የተገለጸውን በመታዘዝና በተግባር በማዋል የእግዚአብሄር መንግስት እንዲሰፋ ምድረን ሁሉ ለክርስቶስ በመማረክ እንድንገዛ እንድናስተዳድር ልንነሳ ይገባል።

እርስበርሳችን ያለንን ህብረት መጠበቅ መቻል አለብን፤ ጉዳዩ ምድራዊ ብቻ አይደለም፤ ሰማያዊም ነው፤ ይልቁንም የጌታ መምጫ በደጅ በሆንበት በአሁኑ ጊዜ ትክክለኛውን ህይወት መኖር እጅግ አስፈላጊና ጊዜ የማይሰጥ ነው፤ ወደ ጌታ በመቅረብ፣ ፊቱን በመፈለግ ከእርሱ በምናገኘው ጸጋ ትዳራችንን ልንመራ፤ ልጆቻችንንም በሚሄዱበት መንገድ ልንመራ እንችላለን፤ ጌታ እየሱስ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም ብሎናልና፣ አይናችንን ከባላችን ላይ አንስተን፣ ከሚስታችን ላይ አንስተን እየሱስ ክርስቶስ ላይ እናሳርፍ፤ ሁሉም በእርሱ ይሰራል፤ ሰላምም ወደ ቤታችን ይገባል፡፡ እንግዲህ ይህ በሁለት ተጋቢዎች መካከል የሚፈጸመው ጋብቻ ቤተስብ የሚለውን ብዜት ይፈጥራል፡፡ ይህ ቤተስብ አላማ ያለው፤ ለምን እንደሚኖር የገባው፤ ጌታ ያለው፤ የሚመራ ያለው፤ ደግሞም ተመልሶ በክብር የሚመጣ ንጉስ ያለው የእግዚአብሄር ቤተሰብ ሆኖ የጌታ የእየሱስ ክርስቶስን ዳግም መምጣት እየተጠባበቀ ጌታ ደስ የሚለውን በመመርመር የዘላለም ህይወትን በመናፈቅ ተግቶ የሚጠብቅ፤ ከአብራኩ የወጡትን ልጆች በእውነት መንገድ የሚመራ፤ለዘላለም መንግስት እንዲበቁ ለማድረግ የማያሰልስ፤ እውነተኛ የክርስቶስ ወዳጅና ለእግዚአብሄር መንግስት በምድር ላይ መስፋፋት ዋጋ ለመክፈል የተሰጠ ተቋም ነው፡፡በአላማ የሚመራ ቤተሰብ ወዴት እንደሚሄድ ስልሚረዳ በምድራዊ ህይወት ውጣ ወረድ መንፈሱ አይረብሽም፡፡ምክንያቱም የቤቱ ራስ ክርስቶስ ስልሆነ በአምላኩ ተማምኖ ይኖራል፡፡ እግዚአብሄር ትዳራችሁን ልጆቻችሁንና ቤተሰባችሁን ሁሉ ይባርክ፡፡